SEATTLE PUBLIC SCHOOLS

AMHARIC

**Advanced Learning**

*Mailing address: M.S. 32-936 – P.O. Box 34165 Seattle, WA 98124-1165*

*Web address*: http://www.seattleschools.org/area/advlearning/index.xml *Phone: 206-252-0130*

# መረጃን የያዘ ጥቅል ፓኬት

## አንድን ልጅ ልቀት ያለው ትምህርት እንዲማር እንዲፈተን እንዴት መምረጥ እችላለሁ ?

ወላጆች፣አስተማሪዎች/ሰራተኞችና የኮሚኒቲ አባላት አንድ ተማሪ እንዲፈተን ሊመርጡ ይችላሉ፤ ነገር ግን ፈተናውን ለመውሰድ የወላጅ የፈቃድ መስጫ ፎርም ተሞልቶ መፈረም አለበት። አስተማሪዎችና የኮሚኒቲ አባላት ለመምረጥ የፈለጉትን ተማሪ ወላጅ የወላጅ ፈቃድ መስጫ ፎርሙን መስጠት ይኖርባቸዋል። የአስተማሪ/ሰራተኛ አስተያየት መስጫ ፎርምም አስፈላጊ ነው። ሁለቱም ፎርሞች ከ ጥቅምት(ኦክቶበር) 8, 2008* በፊት መመለስ አለባቸው። (*ለኪንደርጋርተን ተማሪዎች ብቻ፡ የአስተማሪ/ሰራተኛ ፎርሙ ህዳር 12, 2008፤ የወላጅ ፎርሙ ደግሞ ከጥቅምት 8, 2008 በፊት መመለስ አለበት)

## የመምረጫ ፎርሙን የት ማግኘት እችላለሁ ?

የመምረጫ ፎርሞቹ በአንደኛና በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ጽህፈት ቤት፤ በመመዝገቢያ ጣቢያዎች፤በባይሊንጓል ቤተሰብ ማእከል(252-7750)፤በጆን ስታንፈርድ የትምህርት ማእከል ይገኛል። እንዲሁም ከዚህ ቀጥሎ ባለው ዌብ ሳይት ማግኘት ይችላሉ፤ www.seattleschools.org/area/advlearning/index.xml.

## የመምረጫ ፎርሙን የት ነው መመለስ ያለብኝ ?

የተሞላውን የወላጅ ፈቃድ መስጫ ፎርም ለትምህት ቤትዎ ጸሃፊ ወይም በቀጥታ ከላይ በተጠቀሰው አድራሻ መላክ ይችላሉ። የፈቃድ መስጫ ፎርሙን ለአስተማሪዎች መስጠት የለባችሁም። አስተማሪዎች/ሰራተኞች የአስተያየት መስጫ ፎርሙን ለትምህርት ቤት ጸሃፊዎች መስጠት ወይም በውስጥ መላላኪያ ወይም በፖስታ ቤት በኩል መላክ ይችላሉ። በግል ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች ወላጆች ፎርሞቹን ከላይ ወደ ተጠቀሰው የአድቫንስድ ለርኒንግ አድራሻ ከማይመለስ ከ $90 ዶላር ማመልከቻ ጋር መላክ ይኖርባቸዋል። ፋክስ የተደረገ ወይም ኢሜል የተደረገ ማመልከቻን አንቀበልም።

## ከሲያትል የትምህርት ቤቶች አስተዳደር ክልል ውጭ የምኖር ከሆነ ልጄን ለፈተናው መምረጥ እቻላለሁን ?

አይቻልም። ተማሪዎች በሲያትል ትምህርት ቤቶች አስተዳደር ክልል ውስጥ መኖር ወይም በሲያትል ትምህርት ቤት የሚማሩ መሆን አለባቸው።

## ልጄ የሚፈተንበትን ቀን መቼ እንደሆነ እንዳውቅ እደረጋለሁን ?

የፈተና ቀኖቹ በፈተናው የቀጠሮ መስጫ ደብዳቤ ላይ ይገለጻል። ወላጆች ደግሞ የመጀመሪያውን የቀጠሮ መስጫ ደብዳቤ ከጥቅምት እስከ ታህሳስ መጀመሪያ ባለው ጊዜ ውስጥ ያገኛሉ። የልጆቹ የመጀመሪያ የፈተና ቀን በየክፍሉ ደረጃ ሊለያይ ይችላል።ፈተናው ደግሞ በጥቅምት መጨረሻ አካባቢ ተጀምሮ እስከ ጥር 2009 ይሰጣል። ለወላጆች በሚላከው ደብዳቤ ላይ የፈተናውን ቀንና ምን አይነት ፈተና እንደሚሰጥ ይገለጻል።

## ልጆቻቸው በሚፈተኑበት ወቅት ወላጆች መታዘብ ይችላሉን ?

አይችሉም። ፈተናውን ለሚወስዱት ተማሪዎቻችን ሊረብሽ ይችላል። ተማሪዎች ታዛቢዎች በማይኖሩበት ወቅት የበለጠ እንደሚሰሩ ታውቋል።

## የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች መቼ ነው የሚፈተኑት ?

በአሁኑ ወቅት በሲያትል ትምህርት ቤት የማይማሩ ልጆች የሚፈተኑበት ወቅት ቅዳሜ ነው። የፈተናዎቹ ቦታዎች ደግሞ በተለያዩ የሲያትል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይካሄዳል።የፈተና ቀኖችን የያዘ የቀጠሮ ደብዳቤ ከጥቅምት(ኦክቶበር) አጋማሽ እስከ ታህሳስ ባለው ጊዜ ውስጥ ይላካል።

## የልጄን የፈተና ውጤት መቼ አገኛለሁ ?

የብቁ መሆናቸውን የሚገልጸው የመጨረሻው ውጤትና የፈተና ውጤቶች በጥር(ጃንዋሪ) 16, 2009 አካባቢ ይላካል። ብቁ መሆናቸውንና የፈተና ውጤቶች የሚገለጸው በድብዳቤ ብቻ ነው። አስቀድሞ በቴሌፎን፣ኢሜል ወይም በፋክስ አይገለጽም።

**የመምረጫ ፎርሞች የሚመለስበት ቀን ጥቅምት(ኦክቶበር) 8, 2008 ነው።**

**Advanced Learning**
*Mailing address: M.S. 32-936 – P.O. Box 34165 Seattle, WA 98124-1165*
*Web address*: http://www.seattleschools.org/area/advlearning/index.xml *Phone: 206-252-0130*

### የሚሰጠው የፈተና አይነት ምን አይነት ነው ?

ሁሉም ተማሪዎች የሚሰጣቸው ፈተና (the *Cognitive Abilities Test*). የተሰኘ የእውቀት መለኪያ ፈተና ነው። እንደ ክፍል ደረጃና ብቁነት ታይቶ ደግሞ የንባብና የሂሳብ ፈተናዎች ሊሰጥ ይችላል። የዚህ አይነት ፈተና ከ 4-7 ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች አይሰጥም። ይህ ግን ባለፈው የስፕሪንግ የትምህርት አመት በሲያትል ትምህርት ቤት ያልነበሩትን አይመለከትም። ከ4ኛ እስከ 7 ኛ ክፍል ያሉ የሲያትል ትምህርት ቤት ተማሪዎችን ዋስል በተሰኘው ወቅታዊ ፈተና አማካይነት እንገመግማለን። የዚህ ፈተና ግምገማ በመዝገባቸው ውስጥ የሌላቸው ተማሪዎች አይቲቢኤስ የተሰኘ ፈተና በመስጠት ሊገመገሙ ይችላሉ። በኪንደርጋርተንና በአንደኛ ክፍል የሚገኙ ተማሪዎች ባገኙት የእውቀት መለኪያ ፈተና ምክንያት ተጨማሪ የንባብና የሂሳብ ፈተና የሚያስፈልጋቸው ከሆነ "ውድኮክ ጆንሰን" የተሰኘ ፈተና ይሰጣቸዋል።

### ብቁ ለመሆን የንባብና የሂሳብ የመለኪያ ፈተናዎች ውጤቶችን መስጠት ይቻላል ?

በአሁኑ ወቅት በሲያትል ትምህርት ቤቶች የማይማሩና ነገር ግን የንባብና የሂሳብ በትምህርት ቤት ክልል ሆነው የመለኪያ ፈተና ከመጋቢት (ማርች) 1, 2008 በኋላ የወሰዱ ውጤቶቻቸውን ማቅረብ ይችላሉ። የነጥብ ሪፖርቱ በአድቫንስ ለርኒንግ ጽህፈት ቤት እስከ ታህሳስ(ዲሰምበር) 16, 2008 መሰጠት አለበት። ተቀባይነት እንዲኖረው በአገር ደረጃ ታዋቂ የሆኑ ፈተናዎች እንደ( አይቲቢኤስ, ኢአርቢ) ወይም ከሲያትል ትምህርት ቤት ውጭ የሚማሩ ተማሪዎች የዋስል ፈተና ውጤት መሆን አለባቸው።). የሚቀርበው ውጤት በተማሪው መዝገብ ውስጥ እንዲቀመጥ ይደረጋል። ነገር ግን በእውቀት መለኪያ ፈተና ምትክ ሊሆን አይችልም።

### አንድ ተማሪ ብቁ አልሆነም ተብሎ የተወሰነውን ውሳኔ ይግባኝ ለማለት የሚያስችል አሰራር አለወይ ?

አዎ። የይግባኝን አሰራር የሚመለከት መረጃ በሚላክላችሁ ደብዳቤ ላይ ይገለጻል እንዲሁም በአድቫንስ ለርኒንግ የዌብ አድራሻ ላይ ይገኛል። በግል የተደረጉ ግምገማዎች ይግባኝ በሚባልበት ወቅት ብቻ በግምት ለማስገባት ተቀባይነት ይኖራቸዋል።

### ተማሪዎች ብቁ መሆናቸውን ለማስጠበቅ በየአመቱ መፈተን አለባቸውን ?

ተማሪው በአክሲሌሬትድ ፕሮግሬስ ፕሮግራም(ኤፒፒ)፣ ስፔክትረም ፕሮግራም ወይም አድቫንስድ ለርኒንግ ኦፖርቹኒቲ(ኤኤልኦ) በተሰኙ ፕሮግራሞች የተመዘገበ ከሆነና የአድቫንስድ ለርኒንግ ውጤት የሚያገኝ ከሆነ ብቁነቱን ለማጠበቅ በያመቱ መፈተን አይኖርበትም። ይህም ከ 5ኛ ወደ 6ኛ ክፍል የሚሸጋገሩ ተማሪዎችን ይመለከታል።. በ 2008-2009 የፈተና ወቅት ተፈትነው ብቁ ሆነው የተገኙ ተማሪዎች ፡ በፕሮግራሙ ተመዝግበው <u>ካልተማሩ</u> በሚቀጥለው የፈተና ጊዜ እ<u>ንደገና መፈተን</u> ይኖርባቸዋል። ለፕሮግራሙ ያመለከቱ ተማሪዎችና በመጠባበቅ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ጊዜው ይራዘምላቸዋል ነገር ግን ለሚቀጥለው አመት ወይም ለመፈተን ክፍት ጊዜ በሚኖርበት ወቅት መመዝገብ ይኖርባቸዋል።

### ልጄ በግል ትምህርት ቤት ይማራል። የተማሪ የመታወቂያ ቁጥር ምን መጠቀም አለብኝ ?

ከዚህ በፊት ልጅዎን በሲያትል አብያተ ትምህርት ቤት ለማስመዝገብ አመልክተው ከሆነ ልጅዎ የሲያትል ትምህርት ቤት መታወቂያ ቁጥር አለው። በግል ትምህርት ቤት ልጃቸውን የሚያስተምሩ ወላጆች ስለዚህ ጉዳይ የሚያስታውሱት ነገር ከሌለ ወይም የሲያትል ትምህርት ቤት መታወቂያ ቁጥር ከሌላቸው ይህንን የሚጠይቀውን ክፍል ሳይሞሉ መተው ይችላሉ። እባክዎን ሶሻል ሴኩሪቲ ቁጥራቸሁን አትጻፉበት።

### በመምረጫ ፎርሙ ላይ ለምንድነው የዘር/ጐሳ ጥያቄ የቀረበው ?

በሲያትል አብያተ ትምህርት ቤት መታወቂያ ቁጥር ለመስጠት አስፈላጊ ነው። በአሁኑ ወቅት በሲያትል ትምህርት ቤት ያልተመዘገቡ ተማሪዎችና መታወቂያ* የሌላቸው ደግሞ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል።

*ልጅዎ በሲያትል ትምህርት ቤት በአሁኑ ወቅት ያልተመዘገበ ከሆነና የሲያትል ህዝባዊ ት/ቤት መታወቂያ ቁጥር ከሌለው ከሚቀጥሉት ወስጥ አንዱን መረጡ፤ AI አሜር ኢንዲያን □ AN ኣላስካን ኔቲቭ፣ BL ብላክ(ጥቁር)፣ CH ቻይኒዝ□ EI ኢስት ኢንዲያን□ FI ፍሊፒኖ□ GY ጂፕሲ □ HA ሂስፓኒክ ኤዥያን ወይም ፓስፊክ አይላንደር፣ HB ሂስፓኒክ ብላክ□ HI ሂስፓኒክ ኢንድያን፣ HW ሂስፓኒክ ዋይት፣ ; JN ጃፓኒዝ፣ KO ኮሪያን□ NA ኔቲቭ አሜሪካን ወይም ሌላ ኣላስካን ኔቲቭ፣ OA ሌላ የኤዥያ ወይ ፓስፊክ አይላንደር□ SA ሳሞኣን□ SO ሳውዝ ኢስት ኤዥያን፣ VI ቬትናሚዝ፣ WH ዋይት

**እባክዎን ለተጨማሪ መረጃ ዌብሳይታችንን የመልከቱ፤**
**http://www.seattleschools.org/area/advlearning/index.xml**

የመምረጫ ፎርሞች የሚመለስበት ቀን ጥቅምት(ኦክቶበር) 8, 2008 ነው።



AMHARIC

**Advanced Learning**
*Mailing address: M.S. 32-936 – P.O. Box 34165 Seattle, WA 98124-1165*
*Web address*: http://www.seattleschools.org/area/advlearning/index.xml *Phone: 206-252-0130*

## ልቀት ያላቸው የትምህርት ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች(አድቫንስድ ለርኒንግ) ምንድናቸው ?

የአድቫንስድ ለርኒንግ ፕሮግራሞች ውስብስብ የሆነና ላቅ ያለ ትምህርት ለልዩ ችሎታ ላላቸው ተማሪዎች የሚሰጥ ነው። በዚህ ፕሮግራም የሚማሩ ተማሪዎች ከሁሉም ባህል፣ቋንቋና የሶሻልና የኢኮኖሚ መሰረት ካላቸው የሚገኙ ናቸው። የተለያየ ችሎታና ውጤቶች ያላቸው ናቸው። የፈጠራ ችሎታቸው፣ልዩ አመለካከታቸውና ትኩረታቸው የሚበረታታበት ለየት ያለ ፕሮግራምና አገልግሎት ያስፈልጋቸዋል። ልቀት ያላቸው ትምህርቶች ፕሮግራሞች/ ብቁነትን የሚለካው ፈተና ፡ የኮሌጅ ቦርድ የልቀት ትምህርት ምደባ ፈተናዎችን የሚያካሂደው፤ ልቀት ያለው ትምህርትን የሚከታተለው ጽህፈት ቤት ነው።

| ፕሮግራም | ክፍል | ለብቁነት ፈተና አስፈላጊነት | ስርዓት ትምህርት |
|---|---|---|---|
| ልቀት ያለው ትምህርት ዕድሎች (ALO) | 1-8 | አያስፈልግም | በንባብና በሂሳብ የተፋጠነና የበለጸገ ካሪኩለም |
| ስፔክትረም የወጣት ምሁራን(ስፔክትረም ያንግ ስኮላርስ) | 1-2 | ያስፈልጋል | በንባብና በሂሳብ የተፋጠነ ካሪኩለም(በተለይ ከተመደቡበት ክፍል አንድ ክፍል ከፍ ያለ) |
| ስፔክትረም | 3-8 | ያስፈልጋል | በንባብ(ላንጉጅ አርት)ና በሂሳብ( ከተመደበበት ክፍል አንድ ክፍል ከፍ ላሉት የሚሰጥ) የተፋጠነ ካሪኩለም |
| አክስሌሬትድ ፕሮግሬስ ፕሮግራም (APP) | 1-8 | ያስፈልጋል | በንባብ(ላንጉጅ አርት) እና በሂሳብ ተማሪው በሚያስፈልገው መጠን(በአብዛኛው ከተመደበበት ሁለት ክፍል ላቅ ያለ) የተፋጠነ ካሪኩለም |
| አለም አቀፍ ባካላውሬት | 9-12 | አያስፈልግም | በአለም አቀፍ መልክ የተዘጋጀና የተገመገመ የትምህርት ፕሮግራም ሆኖ ወደ ኮሌጅ ነጥብ ሊያሰጥ የሚችል የተጠናከረ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት |
| አድቫንስድ ፕሌስመንት | 9-12 | አያስፈልግም | በኮሌጅ ቦርድ የሚተዳደርና የኮሌጅን ነጥብ ሊያሰጥ የሚችል የሁለተኛ ደረጃ የተጠናከረ ትምህርት . |

## ልጄን በእነዚህ ፕሮራሞች እንዲማር እንዲመረጥና እንዲፈተን ብፈልግ፥

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ባህርያት በልጅዎ ላይ ማየት ያስፈልጋል

| | |
|---|---|
| የንግግር ችሎታዎች | ✓ ከእድሜው በላይ ከባድ ቃላት ይጠቀማል<br>✓ ያለማቋረጥ ይናገራል፤ ጥያቄዎችን የሚጠይቅ ይመስላል |
| የአስተሳሰብ ችሎታ | ✓ ብዙ ሃሳቦችን ያፈልቃል<br>✓ ለችግሮች ብዙ መፍትሄዎችን ያቀርባል |
| የመማር ባህርያት | ✓ በቶሎ መረጃን ይረዳል፣ የተማረውን ያስታውሳል<br>✓ ከበድ ያሉ ነገሮችን መስራት ይፈልጋል፤ የተለመዱ የቤት/የክፍል ስራዎችን ላይጨርስ ይችላል ምክንያቱም ለሱ ይበልጥ ፍቺ በሚሰጡት ፕሮጀክት ነክ ስራዎች ላይ ጊዜን ማጥፋት ይፈልጋል |
| የመማር ጉጉት | ✓ ሁልጊዜ በተወሰኑ አርእስቶች/ፕሮጀክቶች ላይ ለመስራት በጣም ፍላጐት ያሳድራል<br>✓ ስራን ለማጠናቀቅ ብዙ መመሪያን አይፈልግም ወይም አይጠብቅም፤ እራሱ መርምሮ ማወቅ ይፈልጋል |
| ማህበራዊ ስሜታዊ እድገት | ✓ ለሌሎች ስሜቶች ይጠነቀቃል፣ ፍትህ ያሳስበዋል<br>✓ ስህተት እንዲኖርበት አይፈልግም/ስህተት ሲኖር በቀላሉ ይበሳጫል<br>✓ ከእድሜው በላይ ከሆኑ ተማሪዎች ወይም አዋቂዎች ጋር መነጋገር ይፈልጋል |
| ማንበብ | ✓ የማንበብ ችሎታው ከፍተኛ ነው፣ ከክፍሉ በላይ ያነባል/ ወይም በልጅነት እድሜው ማንበብ ይጀምራል |
| የሂሳብ ችሎታ | ✓ ሂሳብን በጣም ይወዳል፣ ከክፍሉ በላይ ያለ ሂሳብን ይሰራል በህጻንነቱ በቁጥሮች ላይ ፍላጐትን ያሳድራል |

**ለጠጨማሪ መረጃ ዌብ ሳይታችንን በሚከተለው አድራሻ ይጐብኙ**
**http://www.seattleschools.org/area/advlearning/index.xml**

*AMHARIC*

**Advanced Learning**

*Mailing address: M.S. 32-936 – P.O. Box 34165 Seattle, WA 98124-1165*

*Web address*: http://www.seattleschools.org/area/advlearning/index.xml *Phone: 206-252-0130*

# የወላጅ/አሳዳጊ የፈቃድ መስጫ ፎርም

**(ለሁሉም ፈተናዎች ከመሰጠቱ በፊት ይህ የተፈረመ ፎርም መሞላት አለበት)**

| | |
|---|---|
| የተማሪው የአያት ስም　　የመጠሪያው ስም　　የአባት ስም | የሲያትል ትምህርት ቤት መታዊቂያ ቁ(ያስፈልጋል) |
| የወላጅ/አሳዳጊ ስም(ሙሉ ስም ይጻፍ) | የክፍል ደረጃ(08-09) |
| የቤት አድራሻ<br><br>ሲያትል ዋሽንግተን 98___________ | አሁን የሚማሩበት ት/ቤት(08-09) |
| ቴሌፎን ቁጥር | የትውልድ ቀን |
| የኢሜል አድራሻ | ጾታ |
| ልጅዎ በ 504 ፕላን ላይ እንደተጠቀሰው ልዩ ለፈተና የሚያስፈልግ መመቻቸት የሚፈልግ ከሆነ በሳጥኑ ላይ ምልክት በማድረግ የ 504 ፕላኑን ኮፒ ከላይ ወደ ተጻፈው አድራሻ ፈተናው ከመድረሱ በፊት ይላኩት ☐ | በቤት የሚነገረው የመጀመሪያ ቋንቋ |
| ልጅዎ በሲያትል ትምህርት ቤቶች በላቀ የመማር ፕሮግራም ላይ ብቁ ለመሆን ተመርጠ ወይም ተፈትኖ ያውቃልን ? አዎ__በፍጹም___። አዎ ካሉ በመቼ አመት ነው ልጅዎ የተገመገመው ? | * ዘር/ጐሳ |

## *የሲያትል ትምህርት ቤት ተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ*

ልጄ የልቀት የመማር አገልግሎት ፕሮግራም እንዲፈተን እፈቅዳለሁ። የእውቀት መለኪያ ፈተና ለሁሉም ተማሪዎች ይሰጣል። የችሎታ(አችቭመንት) ፈተናም ሊሰጥ ይችላል። ብቁ መሆኑን ለመለየት፣በፕሮግራሙ ያሉትን አማራጭና ይግባኝ የማለት አስራርን በሚመለከት( WAC 392-170-047 ) ማብራሪያ ተሰጥቶኛል።

ፊርማ_______________________________________________________ ቀን________________

## *የግል ትምህርት ቤት ተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ*

ልጄ የልቀት የመማር አገልግሎት ፕሮግራም እንዲፈተን እፈቅዳለሁ። የእውቀት መለኪያ ፈተና ለሁሉም ተማሪዎች ይሰጣል። የችሎታ(አችቭመንት) ፈተናም ሊሰጥ ይችላል። ብቁ መሆኑን ለመለየት፣በፕሮግራሙ ያሉትን አማራጭና ይግባኝ የማለት አስራርን በሚመለከት( WAC 392-170-047 ) ማብራሪያ ተሰጥቶኛል።

ፊርማ_______________________________________________________ ቀን________________

**በአሁኑ ወቅት በሲያትል ትምህርት ቤት የማይማሩ ልጆች ያላቸው ቤተሰቦች የስራ ማስፈጸሚያ የማይመለስ $90 ዶላር ቼክ መጻፍ አለባቸው።**

በ WAC 392-170-04 ህግ መሰረት ፊርማ አስፈላጊ ነው

* እባክዎን የመረጃውን ገጽ ሁለት ይመልከቱ

**ከኪንገርጋርተን እስከ 7ኛ ክፍል ያሉ የወላጅ የፈቃድ ፎርም ጥቅምት 8, 2008 መመለስ አለበት**

**የፈቃድ ፎርሙ ለትምህርት ቤትዎ ጽህፈት ቤት ወይም በቀጥታ ለአድቫንስድ ለርኒንግ ጽህፈት ቤት መላክ ይችላሉ።**